# የኲዊንስላንድ ሁሉንአቀፍባህል የአእምሮ ጤና ማእከል

# ሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አገልግሎት

# የባለጉዳይ መረጃ ዝርዝር

ቀደም ሲል በሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አገልግሎት፤ ሁለት ቋንቋ መናገር ከሚችል የአእምሮ ጤና አማካሪ ጋር ተነጋግረዋል።

ሁለት ቋንቋ የሚናገረው የአእምሮ ጤና አማካሪ ስም ______________________________ ነው።

የሁሉንአቀፍባህል የህክምና አመክሮ አገልግሎት የሚከተሉትን አገለግሎቶች ሁለት ቋንቋ የመናገር ችሎታ ባላቸው አማካሪዎች አማካኝነት ይሰጣል።

- ባህላዊ በሆኑ መገምገሚያዎች፤
- ባህላዊ ጉድዮችን በማስመርኮዝ፤ ስለእርስዎ የአእምሮ ጉዳይ ገለጣ ማድረግ፤
- የግለዎን የጤና እንክብካቤ በሚመለከት እቅድ ማውጣት ወይንም ቀደም ብሎ የተዘጋጀውን የማስተካከል እርዳታ መስጠት፤
- ስለግልዎ የአእምሮ ጤና ጉዳይ መግለጫና ትምህርት በመስጠት የአጭር ጊዜ እርዳታ ማድረግ፤ ናቸው።

## መብትዎን በተመለከተ

የሚከተሉት መብቶች አልዎት፤

- ስለግልዎ የጤና እንክብካቤ መወሰን፤
- በባህልዎ፤ በእድሜዎ፤ በኑሮ ደረጃዎ፤ በፆታዎ፤ በፆታ ምርጫዎ፤ በሃይማኖትዎ ወይንም ባለዎት የፖለቲካ አመለካከት ምክንያት የባለሙያ እርዳታ ያለመነፈግ፤
- ስለሁኔታዎ ወይንም ስለ በሽታዎ፤ በሚናገሩት ቋንቋ እንዲነገርዎት የማድረግ፤
- የሚረዳዎት ግለሰብ (ጓደኛ፤ ዘመድ ወይንም የድጋፍ ሠራተኛ) እንክብካቤዎን በተመለከተ የማሳተፍ፤
- ግለኝነትዎንና ምስጢርዎን የማስከበር፤
- አስፈላጊ ከሆነ፤ አስተርጓሚ እንዲሰጥዎ የመጠየቅ፤
- በሚደረግልዎት ማንኛውም እንክብካቤ ካልረኩ አቤቱታ የማቅረብ መብቶች ናቸው።

## የእርስዎ ሃላፊነት፤

ከአእመሮ ጤና ባለሙያዎቹ በመተባበር እየሠሩ የአእምሮ ጤና እንክብካቤዎን ለመጠበቅ የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይበረታታሉ፤

- ጤናዎን በተመለከተ የሚጠየቁትን ጥያቄዎች በተቻለ መጠን በግልፅ መመለስ፤
- ቀጠሮዎን ማከበር፤ ማክበር ካልቻሉ ደግሞ የጤና ሠራተኛውን መምጣት ያለመቻልዎን ቀደም ብለው መንገር፤
- ህክምናውን ወይንም የህክምንናውን ክንውን በስምምነቱ መሠረት መከታተል። ካልተቻለም፤ ህክምናውን ለምን መከታተል እንዳልቻሉ ለጤና ሠራተኛው መንገር።
- ለጤና እንክብካቤ ሠራተኛው፤ ለተመሳሳይ ችግር ሌላ የጤና እንክብካቤ ሠራተኛ ያዩ እንደሆነ መንገር ናቸው።

ተጨማሪ መረጃ ወይንም ስለገጠመዎት ስጋት ወይንም አቤቱታ ለማድረግ ከፈለጉ፤ የህክምና አገልግሎት አስተባባሪውን ወይንም የኲዊንስላንድ ሁሉንአቀፍባህል የአእምሮ ጤና ማእከል አስተዳዳሪን በስልክ ቁጥር (07) 3240-2833 ወይንም 1800 188 189 (ከብሪዝበን ከተማ ውጭ ከሆኑ) አለበለዚያም በ tccs@health.qld.gov.au የኢሜል መልእክት ይላኩልን።

እንግሊዘኛ መናገር ካልቻሉ 131450 በመደወል ቋንቋዎን የሚናገር አስተርጓሚ በመጠየቅ (07) 3240-2833 እንዲደውሉ ያስደርጉ። (የአስተርጓሚው ክፍያ በማእከሉ ይሸፈናል)

Queensland Government
Queensland Health


የፖስታ ሳጥን ቁጥር 5767፤ በምእራብ ዳርቻ (West End) Q 4101
175 ሜልበርን ጎዳና፣ ደቡብ ብሪዝበን (South Brisbane) Q 4101
ስልክ፤ (07) 3240-2833 ወይንም 1800 188 189 ፋክስ፤ (07) 3240-2282
ኢሜል፤ tccs@health.qld.gov.au


AMHARIC